## አዋጅ ቁጥር ______/2014

## <u>የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ተልዕኮውን በብቃት ለመወጣት እንዲያስችለው ተጨማሪ ስልጣንና ተግባር እንዲኖረው በማስፈለጉ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 804/2005 ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል ።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር____/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ማሻሻያ</u>

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 804/2005 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፤

1/ ከአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (6) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፆች 7፣8፣9፣10፣11፣12 ተጨምረው ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (7) ንዑስ አንቀጽ (13) ሆኖ ተሸጋሽጓል፤

"(7) በአገር ላይ የሚቃጡ የስነ ልቦና ጦርነቶችን የመመከት ሂደት በበላይነት የመምራት፣ የማስተባበር፤"

"(8) የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት፤የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎትን የመምራት፣የማስተባበር፤

"(9) የብሔራዊ ደህንነት ስጋቶችንና አደጋዎች ምላሽ አሰጣጥ ስርዓትን በሃላፊነት የመምራት፤የሚመለከታቸውን አካላትን የማስተባበር፤"

“(10) ከስራው ጋር በተያያዘ ብሔራዊ የመረጃ ማጠናቀሪያና ማከማቻ ቋት የማቋቋም፣የማስተዳደር፤

“(11) ስልጣንና ተግባሩን ለመወጣት የሚያስችሉትን ድርጅቶች የማቋቋም፤ የመቆጣጠር፤”

“(12) በብሔራዊ የደህንነት አጀንዳዎችና ስጋቶች ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠር፤”

2/ ከአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (6) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (7) ተጨምሮ ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (7) ንዑስ አንቀጽ (8) ሆኖ ተሸጋሽጓል፤

“(7) ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመቀናጀት የመረጃና የደህንነት ትንተና ውጤቶች የፍሰትና የስርጭት ስርዓት የማደራጀት፤በበላይነት የመምራት”

3/ የአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1)፣(2)፣(3)፣(4) እና (5) ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ተተክቷል፤

“(1) በጠቅላይ ሚንስትሩ የሚሾሙ ዳይሬክተር ጀነራል እና ምክትል ዳይሬክተር ጀነራሎች፣እና

(2) አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞ ይኖሩታል።”

4/ ከአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ለ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሐ) ተጨምሮ ነባሮቹ ፊደል ተራ (ሐ)፣ (መ)፣(ሠ)፣(ረ) እና (ሰ) እንደቅደም ተከተላቸው ፊደል ተራ (መ)፣(ሠ)፣(ረ)፣(ሰ) እና (ሸ) ሆነው ተሸጋሽገዋል፤

“(ሐ) የአገልግሎቱን የሠራተኞች የደመወዝ ስኬልና የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ሥርዓት አጥንቶ ለመንግስት ያቀርባል፤ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤”

5/ ከአዋጁ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ለ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሐ) ተጨምሮ ነባሩ ፊደል ተራ (ሐ) ንዑስ አንቀጽ (መ) ሆኖ ተሸጋሽጓል፤

“ሐ) ከሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች የሚገኝ ገቢ ፤”

6/ ከአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (1) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ተጨምሮ ነባሮቹ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ሆነው ተሸጋሽጓል፤

" (2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከመረጃና ደህንነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውንና ለደህንነት ስጋት ምንጭ ይሆናሉ ብሎ አገልግሎቱ ያመነባቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ወይም ውስን አቅራቢዎችን በማወዳደር ግዢ ሊፈጽም ይችላል።"

7/ ከአዋጁ አንቀጽ 16 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 17 ተጨምሮ ነባሮቹ አንቀጽ ከ17 እስከ 30 እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 18 እስከ 31 ሆነው ተሸጋሽጓል፤

"17. <u>ስለሠራተኞች አስተዳደር</u>

የአገልግሎቱ ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይመራል። "

8/ ከአዋጁ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (5) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (6) ተጨምሮ ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (6) ንዑስ አንቀጽ (7) ሆኖ ተሸጋሽጓል፤

"(6) ማንኛውም የአገልግሎቱ ሠራተኛ የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን ወይም በቅስቀሳ ላይ መሳተፍ ወይም መሰል ድርጊቶችን መፈፀም አይችልም።"

9/ የአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ተተክቷል፤

" (2) የአገልግሎቱ ሠራተኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰዉ፦

(ሀ) በአገልግሎቱ ወይም በሃላፊው ወይም በሰራተኛው ስም በቃል ወይም በድርጊት ለማታለልና ለማስመሰል የሞከረ ወይም በማታለልና በማስመሰል የማንኛውንም ዜጋ ወይም ተቋም ሰላማዊ እንቅስቃሴ ወይም ዕለታዊ ተግባር ያወከ፤ ወይም

(ለ) በስራው አጋጣሚ ወይም በስራ ስምሪቱ ያወቃቸዉንና ያገኛቸውን ማናቸውንም መረጃ፣ሰነድ ወይም ሪከርድ የተደረገ መረጃ ወይም ምንጭ ያለ ዳይሬክተር ጀነራሉ ፈቃድ የገለፀ እንደሆነ፤አግባብ ባላቸው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ይቀጣል።"

10/ የአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (3) ተሰርዞ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ተጨምሯል።

"(3) ማንኛውም ሰው ከአገልግሎቱ የተሰጠውን መረጃ መጠቀምና ስራ ላይ ማዋል አለበት።

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣(2) ወይም (3) የተመለከቱ ግዴታዎችን ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ያልተወጣ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ይቀጣል"

3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ---- ቀን 2014 ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት